

# የሕሙማን መብት ድንጋጌ በአጭሩ

## በህሙማን መብቶች ሕግ፣ 5756/1996* መሠረት

1. በኃይማኖት፣ ዘር፣ ፆታ፣ ዜግነት፣ የፆታ ዝንባሌ ወይም ብሄር መድሎ ሳይደረግ ለማንኛውም ታማሚ የሕክምና አገልግሎት ይሰጣል።
2. ታካሚው ሙያዊ ብቃት ፣ ጥራት እና ሰብዓዊነት የተሞላበት ያሕክምና አገልግሎት የማግኘት መብት አለው።
3. በድንገተኛ ሁኔታ ጊዜ ሁሉም ሕክምና የሚያስፈልጋቸው ህመምተኞች ሕክምናውን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ  የማግኘት መብት አላቸው።
   በሌሎች ሁኔታዎች ደግሞ - በጤና ጥበቃ ሥርዓቱ በተቀመጠው የአከፋፈል ሥነ-ሥርዓት መሰረት ይከናወናል።
4. የህክምና አገልግሎት፣ አገልግሎት ሰጪው ተቋም ያለው የመጨረሻ አቅም በሚፈቅደው መጠን ይሰጣል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ ይኸ ታካሚውን ወደ ሌላ ቦታ መምራትን ይጨምራል።
5. ወደ ሌላ የሕክምና ሰጪ ወይም የሕክምና ተቋም የተዛወረ ሕመምተኛ፣ ተጨማሪ ትክክለኛ ህክምና ለማግኘት ከቀድሞ አቅራቢዎቹ ሲያገኝ የነበረውን ትብብር የማግኘት መብት አለው።
6. ታካሚዎች የሃኪሙን ስም እና የሥራ ድርሻ የማወቅ መብት አላቸው።
7. ታካሚዎች ሌሎች አማራጮችን የመመልከት እና ከዚህም ጋር በተያያዘ የሕክምና አገልግሎት አቅራቢውን ሙሉ ትብብር የማግኘት መብት አላቸው።
8. በሕክምናው ሂደት የታካሚው ክብር፣ ምስጢራዊነት እና ግላዊነት ሁልጊዜም የተጠበቀ ይሆናል።
9. ሀ. ታካሚዎች ለሕክምናው ፈቃዳቸውን ከመስጠታቸው በፊት የሚያስፈልጋቸውን ጤና ነክ መረጃዎች ሁሉ የማግኘት መብት አላቸው። የታካሚው ፈቃደኝነት (በፅሁፍ፣ በቃል ወይም በአንዳች አገላለፅ) ብዙውን ጊዜ ህክምናውን ለመቀጠል ቅድመሁኔታ ነው።
   ለ. በአንዳንድ የታካሚዎች መብቶች ሕግ ልዩ ሁኔታዎች፣ ሃኪሙ ያለታካሚው ፈቃድ/ወይም ከታካሚው ፈቃድ በተቃራኒ ህክምና ሊሰጥ ይችላል።
10. ታካሚው በሚመርጠው ሁኔታ እርሱን ወክሎ የህክምና ፈቃድ መስጠት የሚችል ወኪል ሊሰይም ይችላል።
11. ታካሚዎች ከሕክምና ታሪክ ማኅደራቸው የሕክምና መረጃዎችን የማግኘት መብት አላቸው። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ይህን መረጃ መስጠት ታካሚውን በፅኑ
12. የሚጎዳ ሆኖ ሲገኝ፣ በጤና ሚኒስቴር የተቋቋመው የሥነ-ምግባር ኮሚቴ ካፀደቀው፣ ሃኪሙ ይህን መረጃ እንዳይሰጥ ይፈቀድለታል።
    ታካሚው ጥያቄ ወይም ቅሬታ ሲኖረው፣ ሁኔታው እንዲመረመር ታካሚው ለሕክምና ተቋሙ አስተዳዳሪ አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው።

## ለታዳጊዎች የሕክምና አሰጣጥ መመሪያ

የሚከተሉት መመሪያዎች ለአቅመ አዳም/ሔዋን ያልደረሱ ታካሚዎች ያለወላጅ ወይም አሳዳጊ እገዛ የሚመጥበትን ሁኔታ ይዳስሳል።

### ከ 14 ዓመት በታች

1. ምርመራ ወይም ሕክምና ለማድረግ የወላጅ ወይም የአሳዳጊን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል።
2. ነታካሚ መብቶች ሕግ በተቀመጠው መሰረት፣ አስቸኳይ የሕክምና ፍላጎት ካልተከሰተ በቀር ማንኛውም አይነት ግላዊነትን የሚነኩ ምርመራዎች ከ14 ዓመት ዕድሜ በታች ባሉ ታዳጊዎች ላይ ማከናወን አይቻልም።
3. የምርመራ ውጤት እና የተጨማሪ ሕክምና ምክሮች ለታዳጊው በሚገባ ቋንቋ መብራራት አለባቸው፤ ለወላጆች የተፃፈ ደብዳቤም በታዳጊው ወይም በታማኝ መልዕክተኛው መላክ አለበት።
4. ታዳጊው ወደክሊኒኩ ከአዋቂ ሰው ወይም በወላጆች ከተፈቀደለት የቤተሰብ አባል ጋር ከመጣ፣ ሃኪሙ አስፈላጊውን መድበኛ ህክምና መስጠት ይችላል።

### ከ 14 ዓመት በላይ

ሃኪሙ ከወላጆች ግልፅ ፈቃድ ባያገኝም በታዳጊው ፈቃድ ህክምናውን ማከናወን ይችላል

የምርመራ ውጤት እና የተጨማሪ ሕክምና ምክሮች ለታዳጊው በሚገባው ቋንቋ መብራራት አለባቸው፤ ለወላጆች የተፃፈ ደብዳቤም በታዳጊው ወይም በታማኝ መልዕክተኛው መላክ አለበት።

ከመደበኛው የተለየ ሕክምና ካስፈለገ፣ ወይም እጅግ ከባድ የጤና እክል እንዳለ ከተጠረጠረ፣ ከወላጆች ጋር ተገናኝቶ መነጋገር እና የእነሱን ፈቃድ ማግኘት ይመከራል። ይህ ካልተቻለ፣ የHMO ይማኅበረሰብ ሰራተኛን እርዳታ መጠየቅ ይቻላል።

ሃኪሙ፣ የታዳጊው የብስለት ደረጃ በእርሱ ዕድሜ ከሚጠበቀው ያነሰ እንደሆነ ከተሰማው፣ ከ14 ዓመት ዕድሜ በታች እንደሆነ ተቆጥሮ ሊታከም ይችላል።

ለሉሚት አባላት መረጃ ለመስጠት የተዘጋጀ

ይህ ሰነድ የታካሚዎች የመብት ሕግ ሰነድን እንደማይተካ ግልፅ ይሁን፤ በዚህ ሰነድ እና በሕጉ ሰነድ መካከል ልዩነት*
ቢታይ፣ የሕጉ ሰነድ ይፀናል።